# <u>ወደ ጥሪው ፍጻሜ የሚገሰግስ አማኝ:- መጠራትንና መመረጥን ማጽናት</u>

## 2 ጴጥሮስ 1፡1-11[1]

የክርስትና ሕይወት ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝ በመቀበል ብቻ የሚቆም አይደለም፡፡ የክርስትና ሕወት መጠራትንና መመረጥን በማጽናት ወደ ጥሪያችንና ወደ ጠሪያችን መገስገስ የሚጠይቅ ሕይወት ነው፡፡ በዘመናችን ኢየሱስን እንዳመኑ የሚናገሩ፣ ወደ ጸሎትና አምልኮ ስፍራዎች የሚመጡ፣ በተለያዩ ዘርፎች እናገለግላለን የሚሉ፣ ወዘተ ነገር ግን በዕለት ከዕለት ሕይወታቸው በእግዚአብሔር መጠራታቸውንና መመረጣቸውን በሚኖሩት ተጨባጭ ሕይወት የማያስመሰክሩ ብዙዎች ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ ከመጨረሻው ዘመን ምልክቶች ዋነኛው ነው፡፡ ጳውሎስ እንዲህ በማለት ተናግሯል፡-

> *ነገር ግን በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን እንዲመጣ ይህን እወቅ፡፡ ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉና፥ ገንዘብን የሚወዱ፥ ትምክህተኞች፥ ትዕቢተኞች፥ ተሳዳቢዎች፥ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፥ የማያመሰግኑ፥ ቅድስና የሌላቸው፥ ፍቅር የሌላቸው፥ ዕርቅን የማይሰሙ፥ ሐሜተኞች፥ ራሳቸውን የማይገዙ፥ ጨካኞች፥ መልካም የሆነውን የማይወዱ፥ ከዳተኞች፥ ችኩሎች፥ በትዕቢት የተነፉ፥ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፤ የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል፤ ከእነዚህ ደግሞ ራቅ፡፡ (2 ጢሞቴዎስ 3፡1-5 - አሮጌው ትርጉም)*

እነዚህ ጥቅሶች አማኞች ነን በሚሉ ሰዎች መካከል ስላለው ሁኔታ የሚናገሩ ናቸው፡፡ አሁንም በዘመናችን እንዲህ ዓይነት ሰዎች በምድር ባለችው በምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ዙርያ ይገኛሉ፡፡ ለዚህ ነው ጳውሎስ፡- ***"ነገር ግን በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን እንዲመጣ ይህን እወቅ"*** በማለት ለጢሞቴዎስ በግልጽ የጻፈለት፡፡ ይህ ዘመን ለቤተ ክርስቲያን፣ በክርስቶስ ፍጹም የሆነ ሰው ለእግዚአብሔር ለማቅረብ ለሚደክሙ አገልጋዮች፣ ለእውነተኛ አማኞች፣ ለቅዱሳን ጉባኤ፣ ቤተ ክርስቲያን ብርሃንነትዋና ጨውነትዋ እንዲገለጥ ለሚፈልጉ፣ የክርስቶስ መልክና ውበት በቤተ ክርስቲያን እንዲታይና በዓለም ተጽዕኖ እንዲያመጣ ለሚፈልጉ፣ ለሕብረተሰብ፣ ለሐገር፣ ወዘተ አስጨናቂ ጊዜ ነው፡፡ ዋነኛው ምክንያቱ ደግሞ የአምልኮ መልክ ያላቸው ነገር ግን የእግዚአብሔርን ኃይል የካዱ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን መብዛታቸው ነው፡፡

የክርስትና ሕይወት ግን ኢየሱስን እንደ አዳኝ በመቀበል የሚያበቃ ሳይሆን በምንኖረው ሕይወት ማለትም መንፈሳዊ ፍሬ እያፈራንና ክርስቶስን በመምሰል እየኖርን ክርስትናችንን በማስመስከር ወደ ጥሪያችንና ጠሪያችን የሚገሰግስ ሕይወት ነው፡፡ በዚህ ትምህርት ውስጥ በ1 ጴጥሮስ 1፡1-11 ላይ መሰረት በማድረግ የምንመለከተው **<u>"ወደ ጥሪው ፍጻሜ የሚገሰግስ አማኝ"</u>** የሚል ርዕስ ሲሆን ዓላማውም አማኞች በእግዚአብሔር መጠራታችንና መመረጣችንን በምንኖረው ተግባራዊ የክርስትና ሕይወት ማጽናት እንዳለብን ለማስገንዘብና ለማሳሰብ ነው፡፡

---

[1] በግልጽ እስካልተጠቀሰ ድረስ በዚህ የትምህርት ማቴርያል ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት ጥቅሶች ከአዲሱ መደበኛ ትርጉም የተወሰዱ ናቸው፡፡

## I. <u>መግቢያ (1፡1-2)</u>

### 1. <u>ጸሐፊ (1፡1ሀ)</u>

*የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይና (ባሪያና) ሐዋርያ ስምዖን ጴጥሮስ፥ (2 ጴጥሮስ 1፡1ሀ)*

የዚህ ክፍል ጸሐፊ ስምዖን ጴጥሮስ ነው። እርሱ ራሱን የክርስቶስ አገልጋይ (ባርያ) እና የክርስቶስ ሐዋርያ እንደሆነ ተናግሮአል (ቁ. 1ሀ)።

### 2. <u>ተደራስያን (የመልእክቱ ተቀባዮች) (1፡1ለ)</u>

*በአምላካችንና በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ በኵል እንደተቀበልነው ዓይነት ክቡር እምነትን ለተቀበሉት፤ (2 ጴጥሮስ 1፡1ለ)*

የመልዕክቱ ተቀባዮች ስምዖን ጴጥሮስና ሌሎች ሐዋርያት ከተቀበሉት ውድና የከበረ እምነት ጋር የተካከለ (እኩል የሆነ) እምነት ያገኙ (የተቀበሉ) አማኞች ናቸው (ቁ. 1ለ)። ይህ እምነት የሚገኘው በአምላካችንና በመድሃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ በኩል ብቻ ነው።

### 3. <u>የባርኮት ቃል፡- የጸጋና የሰላም ብዛት ለምዕመናን ይሁን (1፡2)</u>

*እግዚአብሔርንና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በማወቅ ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ። (2 ጴጥሮስ 1፡2)*

ጴጥሮስ በቁጥር 2 ላይ ለሚጽፍላቸው ሰዎች ጸጋና ሰላም እንዲበዛላቸው ከልብ የሆነ ምኞቱን ይገልጽላቸዋል። ይህ ጸጋና ሰላም የሚበዛው እግዚአብሔርንና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በማወቅ ብቻ ነው። ይህ እውቀት እጅግ በጣም የጠበቀና ግላዊ የሆነ ግንኙነትን ወይም ሕብረትን ከእግዚአብሔርና ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር መኖሩን የሚያመለክት ነው። ከዚህ ውጭ ጸጋና ሰላም በሙላት በሕይወታችን ሊገለጥ አይችልም። የእግዚአብሔርን ጸጋና ሰላም በሙላት መቀበልና መለማመድ የምንችለው ከእግዚአብሔርና ከልጁ ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የጠበቀና ግላዊ የሆነ ግንኙነት/ሕብረት ሲኖረን ነው።

## II. <u>ወደ ጥሪው የሚገሰግስ አማኝ ሕይወት (1፡3-11)</u>

### 1. <u>በክርስቲያን ውስጥ የሚገኘው የመለኮታዊ ባህርይ እውነታ መሰረቶች (1፡3-4)</u>

#### ሀ) <u>ከመለኮት ኃይል ተካፋዮች መሆናችን (1፡3)</u>

*በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን እርሱን በማወቅ ለሕይወትና ለእውነተኛ መንፈሳዊነት የሚያስፈልገንን ሁሉ የመለኮቱ ኃይል ሰጥቶናል። (2 ጴጥሮስ 1፡3)*

ክርስቶስ ወደዚህ ድንቅ ሕይወት የጠራን በገዛ ክብሩና በበጎነቱ ነው። ክብሩና በጎነቱ ደግሞ የእግዚአብሔርን ልዕልና የሚያመለክት ነው። "ክብር" የህልውናውን ልዕልና የሚገልጽ ሲሆን "በጎነት" ደግሞ በተግባር የሚገለጠውን ልዕልናውን ማለትም በሥራ የተገለጠ መልካምነቱን ያመለክታል።

ይህ ሕይወት ደግሞ ከእግዚአብሔር የተቀበልነው እንደመሆኑ መጠን መለኮታዊ ባህርይ አለው። ይህንን ሕይወት በራሳችን ልንኖረው የምንችለው አይደለም። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር መለኮታዊ ኃይል ለአማኞች ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚያስፈልጋቸውን ማንኛውንም ነገር ይሰጣቸዋል። መለኮታዊ ሕይወትን ለመኖር መለኮታዊ ኃይል፣ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል፣ የክርስቶስን ኃይል ተቀብለናል።

የመለኮታዊ ኃይል ምንጭ ደግሞ የሚገኘው ክርስቶስን በማወቅ ነው። የመለኮታዊ ኃይልና የመንፈሳዊ እድገት ምንጭ ክርስቶስን በሙላት ማወቅ ነው።

**ለ) <u>የመለኮት ተስፋ ተካፋዮች መሆናችን (1:4ለ)</u>**

> *በእነዚህ ነገሮች አማካይነት እጅግ ታላቅና ክቡር የሆነውን ተስፋ ሰጥቶናል። (2 ጴጥሮስ 1:4ለ)*

በዚህ ጥቅስ ላይ ***"በእነዚህ"*** የሚለው ቃል የሚያመለክተው ከላይ የተጠቀሱትን የክርስቶስን ***"ክብርና በጎነት"*** ነው። ክርስቶስ ከክብሩና ከበጎነቱ የተነሳ የከበረና ውድ የሆነ መለኮታዊ ተስፋ ሰጥቶናል። ይህ ተስፋ እጅግ ታላቅና ክቡር እንደሆነ ደግሞ በግልጽ ተቀምጧል።

> *እና ግን ጽድቅ የሚኖርበትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር በተስፋ ቃሉ መሰረት እንጠባበቃለን። (2 ጴጥሮስ 3:13)*

*የተስፋ ቃሉ ደግሞ በተለያዩ የመጽሐፍ ክፍሎች በግልጽ ተቀምጧል፦*

> *አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርንም አየሁ፥ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና፥ ባሕርም ወደ ፊት የለም። (ራዕይ 21:1)*
>
> *እነሆ፥ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እፈጥራለሁና የቀደሙትም አይታሰቡም፥ ወደ ልብም አይገቡም። (ኢሳይያስ 65:17)*
>
> *እኔ የምሠራቸው አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ከፊቴ ጸንተው እንደሚኖሩ፥ እንዲሁ ዘራችሁና ስማችሁ ጸንተው ይኖራሉ፥ ይላል እግዚአብሔር፦ (ኢሳይያስ 66:22)*

**ሐ) <u>ከመለኮት ባህርይ ተካፋዮች መሆናችን (1:4ሀ)</u>**

> *ከክፉ ምኞት የተነሳ በዓለም ካለው ምግባረ ብልሹ ሕይወት አምልጣችሁ ከመለኮት ባህርይ ተካፋዮች እንድትሆኑ፤ (2 ጴጥሮስ 1:4ሀ)*

ይህ ከላይ የጠቀስነው መለኮታዊ ተስፋ አማኞች የመለኮት ባህርይ ተካፋዮች እንዲሆኑ አስችሏቸዋል። ይህ አማኞች የመለኮትን ተፈጥሮ ይወርሳሉ ለማለት ሳይሆን እግዚአብሔር በእነርሱ ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በእነርሱ ውስጥ ስለሚያድርና ስለሚኖር ወደ አማኞች የሚተላለፉ የእርሱን ባህርያት ይካፈላ ማለት ነው።

አማኞች የእግዚአብሔር ባህርይ ተካፋዮች ከመሆናቸው የተነሳ በዚህ ኃጢአተኛ ዓለም ሲኖሩ በኃጢአት ላይ ድል በመንሳትና በሞት ላይ ድል በመቀዳጀት መኖር ይችላሉ። ከተሰጣቸው የአዲስ ልደት ተስፋ፣ በእግዚአብሔር ኃይል የመጠበቅ ተስፋ እንደዚሁም በእግዚአብሔር የማስቻል ኃይል ተስፋ የተነሳ አማኞች ከመለኮታዊ ባህርይ ተካፋዮች መሆን ይችላሉ።

<u>የአዲስ ልደት ተስፋ፦</u>

> *እርሱ (እግዚአብሔር) ከታላቅ ምህረቱ የተነሳ በኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት መነሳት ምክንያት ለሕያው ተስፋ በሚሆን አዲስ ልደት ... ወለደን። (1 ጴጥሮስ 1:3)*

<u>በእግዚአብሔር ኃይል የመጠበቅ ተስፋ፦</u>

> *እናንተም በመጨረሻው ዘመን ሊገለጥ የተዘጋጀው ድነት እስኪመጣ ድረስ በእምነት አማካይነት በእግዚአብሔር ኃይል ተጠብቃችኋል። (1 ጴጥሮስ 1:5)*

<u>የእግዚአብሔር የማስቻል ኃይል ተስፋ፦</u>

> *በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን እርሱን በማወቅ ለሕይወትና ለእውነተኛ መንፈሳዊነት የሚያስፈልገንን ሁሉ የመለኮቱ ኃይል ሰጥቶናል። (2 ጴጥሮስ 1:3)*

የመለኮታዊ ባህርይ ተካፋይ መሆን የሚያመለክተው ክርስቶስን መምሰል ነው።

> *እናንተ ግን፣ የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጣችሁ የሚኖር ከሆነ፣ በሥጋ ሳይሆን በመንፈስ ናችሁ። ማንም የክርስቶስ መንፈስ ከሌለው፣ እርሱ የክርስቶስ መንፈስ አይደለም። (ሮሜ 8:9)*



በመምህር ማዕረጌ ሐብቱ
+251 911 47 58 42

*ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ፤ ከእንግዲህ እኔ አልኖርም፤ ነገር ግን ክርስቶስ በውስጤ ይኖራል። አሁንም በሥጋ የምኖረው ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን አሳልፎ በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለኝ እምነት ነው። (ገላትያ 2፡20)*

አማኞች የመለኮታዊ ባህርይ ተካፋዮች ስለሆኑ ከክፉ ምኞት የተነሳ በዓለም ካለው ምግባረ ብልሹ ሕይወት ማምለጥ ይችላሉ።

2. **<u>በክርስቲያን ውስጥ የሚገኘው የመለኮታዊው ባህርይ ተግባር ምንድን ነው? (2 ጴጥሮስ 1፡5-9)</u>**

*ሀ)* **<u>በሕይወታችን መንፈሳዊ ፍሬ እንድናፈራ ያደርጋል (1፡5-7)</u>**

*ስለዚህም ምክንያት ትጋትን ሁሉ እያሳያችሁ በእምነታችሁ በጎነትን ጨምሩ፥ በበጎነትም እውቀትን፥ በእውቀትም ራስን መግዛት፥ ራስንም በመግዛት መጽናትን፥ በመጽናትም እግዚአብሔርን መምሰል፥ እግዚአብሔርንም በመምሰል የወንድማማችን መዋደድ፥ በወንድማማችም መዋደድ ፍቅርን ጨምሩ። (2 ጴጥሮስ 1፡5-7 - አሮጌው ትርጉም))*

አማኞችን ከማያምኑት የሚለያቸው ዋናው ነገር በክርስቶስ የሚገኘው እምነት ነው። በክርስቲያን ሕይወት የሚገኙት ባህርያት በሙሉ መሰረታቸው በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ መጨመራችን ነው። ስለዚህ እምነት መሰረታዊ ነገር ነው። ከዚህ የተነሳ ሌሎች ባህርያት በሙሉ በዚህ እምነት ላይ እየተገነቡ ይሄዳሉ።

አማኝ በእምነቱ ላይ ሊጨምራቸው የሚገቡ ባህርያትን ከቁጥር 5-7 ባለው ክፍል ውስጥ ዘርዝሯቸዋል። እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡-

- **በጎነት**፡- ይህ ሞራላዊ ልቀትን የሚያመለክት ነው።
- **እውቀት**፡- ይህ በጭንቅላት ላይ የሚከማች መረጃ ሳይሆን ከመንፈስ ቅዱስ የሚገኝና በእግዚአብሔርና በቃሉ ላይ የሚያተኩር ነው።
- ***ራስን መግዛት***፡- ለክርስቲያናዊ ጉዞ እምነት፣ በጎነትና መንፈሳዊ እውቀት ብቻቸውን በቂ አይደሉም። ክርስቲያን መንፈሳዊ ጉዞውን ለመቀጠል ራስን መግዛት በሕይወቱ ሊለማመድ ይገባዋል። ራስን መግዛት ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ ለሚያስወጡን የዓይን አምሮትና የሥጋ ምኞት "እምቢ" የሚል ምላሽ መስጠት ነው። ስሜቶቻችንና የውስጥ ፍላጎቶቻችንን መግታት መቻል ነው። በመጠን መኖር ነው።
- ***መጽናት***፡- በዚህ ፈተና በበዛበት ኃጢአተኛ ዓለም ሳይናወጡና እጅ ሳይሰጡ በእምነት መቆም መቻል ነው። አማኝ በዚህ ዓለም እንደ መጻተኛ ሲኖር በፊቱ የሚመጡትን ተግዳሮቶችና ፈተናዎች እየተቋቋመ በጽናት ሊሻገር ይገባዋል።
- **እግዚአብሔርን መምሰል/እውነተኛ መንፈሳዊነት**፡- ይህ በእግዚአብሔር ቃልና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የእግዚአብሔርን ባህርይ መልበስ ወይም ክርስቶሳዊ ባህርይ በሕይወታችን መገለጡን የሚያመለክት ነው።
- **የወንድማማች መዋደድ/ወንድማዊ መተሳሰብ**፡- ከላይ የጠቀስናቸው አምስቱ ባህርያት ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት የሚያመለክቱ ውስጣዊ ማንነታችንን የሚያሳዩ ናቸው። የሚከተሉት ሁለት ባህርያት ግን ከሌሎች ጋር ያለንን ግንኙነት የሚያሳዩ ናቸው። የወንድማማች መዋደድ በተግባር የሚገለጥ የአማኞች አንዱ ለሌላው ማሰብንና መደጋገፍን የሚያሳይ ነው።
- **ፍቅር፡-** ይህ ደግሞ ለወንድሞቻችን የተሻለውን ነገር ሁሉ መመኘትና ራሳችንን ለሌሎች መስጠት ነው። ይህ ፍቅር ክርስቶስ ከእኛ ምንም ነገር ሳይጠብቅ ራሱን ለእኛ የሰጠበትን ፍቅር፤ ለእኛ የገለጠው ዓይነት ፍቅር ነው።

እነዚህ ከላይ የዘረዘርናቸው ክርስቲያናዊ ባህርያት በእምነት ላይ የተመሰረቱ፤ ክርስቶስን በመምሰል የተገለጡና በፍቅር የታሰሩ ናቸው።

### ለ) <u>*መንፈሳዊ ፍሬ ውጤት አለው* (1:8)</u>

ከቁጥር 5-7 የዘረዘርናቸው ባህርያት/ፍሬዎች/ ክርስቲያናዊ እድገትን የሚያመለክቱ ናቸው። ክርስቲያናዊ እድገት የመንፈሳዊ ሕይወት መትረፍረፍን፣ መብዛትንና ፍሬያማ መሆንን ያስከትላል።

> *እነዚህ ባህርያት ተትረፍርፈው ቢኖሯችሁ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በማወቅ ዳተኞችና ፍሬ ቢሶች (ineffective and unproductive) ከመሆን ይጠብቋችኋል። (2 ጴጥሮስ 1:8)*

ይህ ***"ቢኖሯችሁ"*** የሚለው ቃል እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ሰባት ባህርያት/ፍሬዎች/ በክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ለመሆናቸው የሚያስረዳ ነው። ነገር ግን የእግዚአብሔር ፍላጎት እነዚህ ባህርያት በውስጣችን መኖራቸው ብቻ ሳይሆን እጅግ እንዲትረፈረፉና በሙላት እንዲገለጡ ጭምር ነው። እነዚህ ባህርያት በሕይወቱ ያልተትረፈረፈለትና ያልበዛለት አማኝ ኢየሱስ ክርስቶስን በግሉ በሚገባ አለማወቁን ያመለክታል። በጣም የሚያሳዝነው ብዙ አማኞች ከዳግም ልደት ወይም የድነት እውቀት ያለፈ ኢየሱስ ክርስቶስን በግላቸው አለማወቃቸው ነው። ብዙ ክርስቲያኖች ኢየሱስን እንደ አዳኛቸው ተቀብለውታል ነገር ግን መንፈሳዊ ፍሬ የላቸውም። መንፈሳዊ ፍሬ የሌላቸው አማኞች ደግሞ መንፈሳዊ እድገት አያሳዩም። ሁልጊዜ በጌታ ሕጻናት ናቸው። ሁልጊዜ ወተት የሚጠጡ ናቸው። ራሳቸውን ችለው መንፈሳዊ ጉዞን መጓዝና መራመድ አይችሉም።

ነገር ግን ጴጥሮስ እንደሚያስተምረን አማኞች በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት ማደግ አለባቸው። የዚህ እድገት ምልክት ደግሞ ከላይ የተመለከትናቸው ክርስቲያናዊ ባህርያት ወይም መንፈሳዊ ፍሬ ነው።

### ሐ) <u>*መንፈሳዊ ፍሬ የማያፈራ ክርስቲያን ኪሳራ ውስጥ ነው* (1:9)</u>

> *እነዚህ ባህርያት የሌሉት ግን የሩቁን የማያይ ወይም ዕውር ነው፤ ከቀድሞው ኃጢአቱ መንጻቱንም ረስቷል። (2 ጴጥሮስ 1:9)*

ከመንፈሳዊ ክርስቲያን ጋር ሲነጻጸር ሥጋዊ ክርስቲያን ዕውርና የሩቁን ማየት የማይችል ነው። መንፈሳዊ ዕውርነት ያለበት ሰው ደግሞ የክርስቶስን ጸጋ ማድነቅና እንደ እግዚአብሔር ሐሳብና ፈቃድ ለመኖር አይችልም። በ 1 ጴጥሮስ 1:5-7 ያሉት የመንፈሳዊ ክርስቲያን መለኪያ የሆኑት ባህርያት/ፍሬዎች/ በሕይወቱ ውስጥ ስለማይታዩና ስለማይገለጡ መንፈሳዊ ዕውርነት እንዳለበት ወይም እንዳልዳነ ሰው ዓይነት ሕይወት ይኖራል።

ይህ ብቻ ሳይሆን እንዲህ ዓይነት ሰው ከቀደመው ኃጢአቱም መንጻቱን ፈጽሞ ረስቷል። ጳውሎስ ለቲቶ የጻፈውን እንዲህ የሚለውን ቃል ዘንግቷል፦

> *እንደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ፥ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለ ነበረው ሥራ አይደለም፤ (ቲቶ 3:5 - አሮጌው ትርጉም)*

ከዚህ የተነሳ እንደ ጥሪው በቅድስናና በጽድቅ፤ መንፈሳዊ ፍሬ በማፈራት ሳይሆን፤ እንዳልዳነ/ድነትን እንዳልተቀበለ/ ሰው በኃጢአት፣ በሥጋዊነትና የሥጋ ስራዎችን በመለማመድ ይመላለሳል።



በመምህር ማዕረጌ ሐብቱ
+251 911 47 58 42

3. <u>በክርስቲያን ውስጥ የሚገኘው መለኮታዊ ባህርይ ወደ ፍጻሜ ገስጋሽ ነው (1፡10-11)</u>
ክርስቲያን ከመንፈሳዊ ዕውርነት በመራቅ ፍሬያማና የተትረፈረፈ ክርስቲያናዊ ሕይወት ለመኖር የመዳኑን እርግጠኝነት በሚገባ ማወቅ አለበት፡፡ ይህ የሚገለጸው በክርስቶስ አዲስ ሕይወት በመኖራችን ወይም መንፈሳዊ ፍሬ በማፍራታችን ነው፡፡

ሀ) <u>ክርስቲያን በዚህ ምድር የሕይወት ልምምድ ወደ ፍጻሜ መገስገስ አለበት (1፡10)</u>

*ስለዚህ ወንድሞች ሆይ፤ መጠራታችሁንና መመረጣችሁን ለማጽናት ከፊት ይልቅ ትጉ፤ ምክንያቱም እነዚህን ብታደርጉ ከቶ አትሰናከሉም፡፡ (2 ጴጥሮስ 1፡10)*

አማኝ ክርስቶስን የሚመስል ባህርይ ወይም እግዚአብሔርን የሚመስል ሕይወት መኖሩ ክርስቶስ ካለፈው ኃጢአቱ እንዳነጻውና በእግዚአብሔር መጠራቱና መመረጡ ማረጋገጫ ነው፡፡ አማኝ በእግዚአብሔር ለመመረጡ ማረጋገጫው በ 2 ጴጥሮስ 1፡5-7 ያሉትን ክርስቲያናዊ ባህርያት ወይም መንፈሳዊ ፍሬ በሕይወቱ መገለጡ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ የሚከናወን ድንቅ የእግዚአብሔር ጸጋ ሥራ ነው፡፡

*ይህም ተስፋ እንደ ነፍስ መልሕቅ አለን እርሱም እርግጥና ጽኑ የሆነ ወደ መጋረጃውም ውስጥ የገባ ነው፤ (ዕብራውያን 6፡9 - አሮጌው ትርጉም)*

*እኛም የምንደፍርበትን የምንመካበትንም ተስፋ እስከ መጨረሻው አጽንተን ብንጠብቅ ቤቱ ነን፡፡ ... የመጀመሪያ እምነታችንን እስከ መጨረሻው አጽንተን ብንጠብቅ፥ የክርስቶስ ተካፋዮች ሆነናልና፤ (ዕብራውያን 3፡6፤14 - አሮጌው ትርጉም)*

ለ) <u>ይህ ሕይወት ወደ ዘላለማዊ ፍጻሜ ሙላት የሚደርስ ነው (1፡11)</u>

*በዚህም ወደ ጌታችንና አዳኛችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘላለማዊ መንግስት መግባት በሙላት ይሰጣችኋል፡፡ (2 ጴጥሮስ 1፡11)*

በክርስቲያናዊ ሕይወቱ ያደገ (መንፈሳዊ እድገት የተገለጠበት) እና እግዚአብሔርን የሚያስከብር ሕይወት የሚኖር ክርስቲያን ሽልማቱ እጅግ ከፍ ያለ ነው፡፡ ይህም በእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ጌታችንና አዳኛችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘላለማዊ መንግስት በክብር መግባቱ ነው፡፡ ከዚህ የሚበልጥ ፍጻሜ ምን አለ!

እስጢፋኖስ ይህንን ሕይወት በሚገባ ተለማምዶታል፡፡ እስጢፋኖስ በሐዋርያት ሥራ 7፡56 በሕይወቱ ፍጻሜ ላይ እንዲህ አለ፡-

*እነሆ፥ ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ አለ፡፡ (አሮጌው ትርጉም)*

ጳውሎስም ክርስቶስን በመምሰል እግዚአብሔርን የሚያስከብር ሕይወት የሚኖሩ ሰዎች በሙሉ ወደዚህ ክብር እነደሚገቡ ማለትም ወደ ዘላለማዊው መንግስት መግባት እንደሚሆንላቸው በግልጽ ተናግሯል፡፡

*መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፥ ሩጫውን ጨርሼአለሁ፥ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ፤ ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፥ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል፥ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም፡፡ ... ጌታም ከክፉ ነገር ሁሉ ያድነኛል ለሰማያዊውም መንግሥት ይጠብቀኛል፤ ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን፡፡ (2 ጢሞቴዎስ 4፡7-8፤18 - አሮጌው ትርጉም)*

ይህ ወደ ጌታችንና አዳኛችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘላለማዊ መንግስት መግባት ደግሞ የሚከናወነው በሙላት ነው፡፡ ይህ ክስተት እግዚአብሔር እርሱን በመምሰልና እርሱን

የሚያስከብር ሕይወት ለኖሩ ልጆቹ በሙሉ በደ ቤቱና ወደ ዘላለማዊው መንግስቱ ***"እንኳን ደህና መጣችሁ!"*** በማለት በደስታ የሚቀበልበት ጊዜ ነው፡፡

አማኞች በሙሉ መንፈሳዊ ፍሬ በማፍራትና ክርስቶስን በመምሰል በዚህ ኃጢአተኛ ዓለም እየኖሩ ለዚህ ድንቅ ጊዜ ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ ሐዋርያው ጴጥሮስ ይጋብዛል፡፡ ስለዚህ እኛ አማኞች መጠራታችንንና መመረጣችንን በማጽናት ወደ ጥሪያችን ፍጻሜ ልንገሰግስ ይገባናል፡፡